የሰ.መ.ቁ 207341

ቀን የካቲት 28 2014ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ዳኞች፡ ተፈራ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡ የጉምሩክ ኮሚሽን የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪ፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈ ምስራቅ ክፍሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 282586 በ26/2/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 261217 በ8/7/13ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ6/9/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው።

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ የተጠሪ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ተበዳሪ የነበረው ኢናሻ ፓኬጂንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከባንኩ የወሰደውን የብድር ገንዘብ እንደውሉ ባለመክፈሉ ባንኩ ለብድሩ በመያዣነት የያዘውን በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 01 በይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር 478/21 የሚታወቀውን ፋብሪካ ህንጻ እና ማሽነሪዎች በአ/ቁ 97/98 እና 98/90 መሰረት በ28/3/08ዓ.ም በጨረታ ለብሉናይል የፒፒና ክራፍት ወረቀት ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሸጧል። ኢናሻ ፓኬጂንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለብድሩ መያዣ የሰጣቸው የፋብሪካውን ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነጻ ወደ ሀገር ያስገባ በመሆኑ የአ/ቁ 859/2006 አንቀጽ 130(2) በደነገገው መሰረት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ ወደ ሀገር የገባ እቃ ተመሳሳይ የቀረጥና ታክስ ነጻ መብት ላለው ሰው/ድርጅት ሊተላለፍ እንደሚችል በሚገልጸው መሰረት ገዥው ድርጅት ከቀረጥ ነጻ የመጠቀም መብቱን በመጠቀም በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት አስፈላጊውን ሂደት በማከናወን ከቀረጥ ነጻ የገቡትን እና ለብድሩ መያዣ የሆኑት ማሽነሪዎች ብቻ የስም ዝውውሩን አከናውኗል።

የስም ዝውውሩ ከተከናወነ በኋላ አመልካች ለተጠሪ በተደጋጋሚ በጻፈው ደብዳቤ ኢናሻ ፓኬጂንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የቀረጥና ታክስ እዳ አስተዳደራዊ ቅጣት ተካትቶ ብር 32,605,678.74(ሰላሳ ሁለት

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 29-6-14

ሚሊዮን አምስት መቶ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ አራት ሺህ ብር ከሰባ አራት ሳንቲም) የሚፈለግበት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ባንኩ የብድር መያዣ ያደረጋቸውን ከቀረጥ ነጻ የገቡ ማሽነሪዎችን ብሉናይል የፒፒና ክራፍት ወረቀት ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም ሲያዛውር ያቀረበው ዝርዝር ተቀንሶ ብር 29,122,264.49(ሀያ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ሀያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አራት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሳንቲም) ቀረጥ እና ታክስ የሚፈለግበት በመሆኑ ተጠሪ ተመሳሳይ መብት ተጠቃሚ ከሆነ ዲክላራሲዮን በመሙላት ስም እንድናዛውር ካልሆነ ክፍያ እንድንፈጽም ጠይቆናል። አመልካች ይህን ጥያቄ የጠየቀው በኢኖቫ ፓኬጂንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም ከቀረጥ ነጻ የገቡ ማሽነሪዎች ነገር ግን ተጠሪ ለብድር በመያዣ ያልያዛቸው እንዲሁም በሽያጭ ወደ ብሉናይል የፒፒና ክራፍት ወረቀት ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ወይም ወደ ሌላ ማንኛውም ሶስተኛ ወገን ያላስተላለፋቸው በመሆኑ ከነዚህ ማሽነሪዎች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተጠሪን የማይመለከቱ መሆኑን ተጠሪ ለአመልካች በተደጋጋሚ ቢያሳውቅም እንዲሁም በአመልካች መስሪያ ቤት በአካል ቀርቦ ቢያስረዳም የአመልካች ክፍያ ይፈጸምልኝ ጥያቄ አልቆመም።

አመልካች በኢኖቫ ፓኬጂንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም ከቀረጥ ነጻ ወደ ሀገር የገቡ ማሽነሪዎች በሙሉ የተጠሪ ኃላፊነት በማስመሰል ከህግ ውጪ ተጠሪን በማይመለከተው ጉዳይ ክፍያ እንዲፈጽም በተደጋጋሚ በመጠየቅ እና ክፍያ የማይፈጸምለት ከሆነ ግን የተጠሪን ንብረቶች እንደሚወርስ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የተጠሪን የእለት ተእለት ስራ በማወክ ላይ ይገኛል። ስለሆነም የአመልካች ድርጊት የሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል። ማስረጃዎችንም አቅርቧል።

አመልካች ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149 እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 80241(ቅጽ 15) በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት ሁከት ተፈጥሯል ለማለት የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን አያሟላም። ተጠሪ ሁከት የተፈጸመበት በማስመሰል ያቀረበው ክስ መነሻው የተጠሪ ደንበኛ የሆነው ኢኖቫ ፓኬጂንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተጠሪ ለወሰደው ብድር የድርጅቱን ንብረቶች በዋስትና በመያዙ ምክንያት የድርጅቱ ንብረቶች ከቀረጥ ነጻ የገቡ በመሆኑ በንብረቶቹ ላይ መንግስት የሚፈልገውን ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው። አመልካች በተጠሪ ላይ የቀረጥና ታክስ ክፍያ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የሰጠውም ተጠሪ በህግ አግባብ መክፈል የነበረበትን ቀረጥና ታክስ ባለመክፈሉ ነው። ይህም የሚያሳየው በተጠሪ እና በአመልካች መካከል አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የቀረጥና ታክስ ክፍያ መሆኑን ነው።

የቀረጥና ታክስ ክፍያ ጉዳይ በዋናኛነት በጉምሩክ አ/ቁ 859/06 የሚሸፈን ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 152-154 ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት ጉዳዩን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ያለው የአመልካች መስሪያ ቤት ነው። ይኸውም ተጠሪ ከፊል በተባለው ቀሪ የቀረጥ[illegible] ክፍያ ላይ ቅሬታ

ፌ.ደ.ራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ Sut ቀን 29-6-1[illegible]

ካለው ቅሬታውን በአዋጁ አንቀጽ 152 እና 153 በተቀመጠው መሰረት ባለስልጣኑ በየደረጃው ባቋቋመው የአቤቱታ አጣሪ ስራ ክፍል ፊት በቅድሚያ ሊቀርብ ይገባል። በዚህም መሰረት ተጠሪ ቅሬታውን በአዋጁ አንቀጽ 153(1) መሰረት ለባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት አቤቱታ አጣሪ እና በአንቀጽ 153(2) መሰረት ለዋናው መስሪያቤት አቤቱታ አጣሪ ማቅረብ ነበረበት። በነዚህ አካላት ውሳኔ ቅር ከተሰኘም በአዋጁ አንቀጽ 155 መሰረት ለፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርቦ መዳኘትና የህግ ስህተት ካለ ደግሞ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊያቀርብ ይገባል እንጂ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚቀርብበት የህግ መሰረት የለም። ተጠሪ ይህን የህግ ስርአት ሳይከተል በቀጥታ ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት በመውሰድ ክስ ማቅረብ የሚችልበት የህግ መሰረት የለም። በተጨማሪም በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 86817(ቅጽ15) በሰጠው ውሳኔ ከቀረጥና ታክስ ክፍያ ጋር የተያያዙ ክርክሮችን መደበኛ ፍ/ቤቶች በቀጥታ የማየት የስረነገር ስልጣን የላቸውም ሲል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ ፍ/ቤቱ የተነሳውን የቀረጥና ታክስ ክፍያ ጉዳይ በቀጥታ የማየት የስረነገር ስልጣን አለው ከተባለም ጉዳዩን በይግባኝ ደረጃ የማየት ስልጣን ያለው የከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። ስለሆነም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የመጀመሪያ ደረጃ የስር ነገር ስልጣን የሌለው በመሆኑ የተጠሪ ክስ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል።

አመልካች ፍሬጉዳዩን በተመለከተም የክርክር ነጥቦችን በማንሳት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል። ማስረጃዎችንም አያይዟል።

ፍ/ቤቱም በመቃወሚያው ላይ ክሱን ከሰማ በኋላ አመልካች ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የመጀመሪያ ደረጃ የስረነገር ስልጣን የለውም ሲል ያቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(1) በደነገገው ላይ ሁከት የተነሳበት ሰው የተነሳው ሁከት በፍርድ ሀይል እንዲወገድለት መጠየቅ እንደሚችል የደነገገ ሲሆን በጉምሩክ አ/ቁ 859/06 አንቀጽ 152 እና ተከታዮቹ ላይ እንደተገለጸው አመልካች በጉዳዩ ላይ ስልጣን የሚኖረው በእቃዎች የስሪት አገር አወሳሰን፤ ዋጋ አተማመን፤ አሰያየም፤ አመዳደብ፤ በታሪፍ ልክ እና በአዋጁ በተካሄዱ ድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲትን ተከትሎ በተሰጡ ውሳኔዎች እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 2(ለ)(ሐ) ከተመለከቱት ውጪ በሆኑ ከጉምሩክ ፎርማሊቲ ጋር በተያያዘ በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን የተመለከተ እንደሆነ ተደንግጓል።

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው አመልካች በቁጥር አቃ ጉ201/066/530 በ21/10/10ዓ.ም ለተጠሪ የጻፈው ደብዳቤ ነው። አመልካች በዚህ ደብዳቤ ተጠሪ ለብድር ማስመለሻ በዋስትና የያዘውን የፕላስቲክ ከረጢት እና የፌስታል ማምረቻ ፋብሪካን ለመሸጥ በእንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ገልጸው ባንኩ ገንዘቡን እንዲከፍል የተጻፈ ሲሆን ተጠሪ በክሱ ያቀረበው ክርክር አመልካች በደብዳቤው የጠየቀውን ሳይሆን ተጠሪ ለብድር መክፈያነት በመያዣነት ያልያዛቸው እንዲሁም በሽያጭ ወደ ባንኩ ያልገቡ የፒፒና

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
29-6-11

ከራፍት ወረቀት ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ወይም ወደ ሌላ ማንኛውም ሶስተኛ ወገን ያሳስተላለፋቸው ንብረቶች መሆኑን በመግለጽ የሁከት ተግባሩ ሊወገድ ይገባል የሚል ዳኝነት እንጂ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 ስር ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ጋር የሚገናኝ አይደለም። ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፋቸው ንብረቶች ከቀረጥ ነጻ የገቡ ስለመሆናቸው በፍሬነገር ክርክር የሚባሉ ሆኖ ጉዳዩን ፍ/ቤቱ የማየት ስልጣን ያለው በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም በማለት ብይን ሰጥቷል።

ከዚህ ሂደት በኋላ ፍ/ቤቱ ወደ ፍሬጉዳዩ በመግባት ክሱን ሰምቶ፣ በግራቀኙ የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ አመልካች ተጠሪ ከላይ የተገለጸውን ክፍያ እንዲፈጽምለት ወይም ተጠሪ ተመሳሳይ የቀረጥ ነጻ መብት ተጠቃሚ ከሆነ ዲክላራሲዮን በመሙላት የስም ዝውውር እንዲያከናውን ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሁከት ተግባር ነው በማለት ሁከቱ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(1) መሰረት ሊወገድ ይገባል በማለት ወስኗል።

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል።

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔ እና ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ማንኛውም ከጉምሩክ ስነ ስርአት ጋር በተያያዘ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው አካል አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት ሳይሆን በህግ በተዘረጋው የይግባኝ ስርአት መሆኑ በአ/ቁ 859/2006 አንቀጽ 153 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ተመልክቷል። የይግባኝ አቀራረብ ስርአቱም ጉዳዩ ከአመልካች መስሪያ ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቀርቦ ከታየ በኋላ ቅሬታ ያለው ወገን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ (ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን) ማቅረብ እንዳለበት፣ ከዚያም የተፈጸመ የህግ ስህተት ካለ በአዋጁ አንቀጽ 155(3) መሰረት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት፣ በዚህም ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን በአዋጁና በኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና የፌ/ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አ/ቁ 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረት ለበላይ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ ይግባኙን እና የሰበር አቤቱታውን ማቅረብ እንደሚችል የድንጋጌዎች አቀራረጽና ይዘት ያሳያል። ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች የቀረጥና ታክስ ክፍያ ጥያቄ አግባብነት የለውም የሚለው የተጠሪ ክርክር በነዚሁ አዋጆች በተዘረጋው ስርአት መሰረት ታይቶ እልባት ከሚያገኝ በስተቀር በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት የሚቀርብበት እና የስር ፍ/ቤትም ጉዳዩን በቀጥታ አይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ አይኖርም።

ተጠሪ ሁከት የተፈጸመበት በማስመሰል ያቀረበው ክስ መነሻው የተጠሪ ደንበኛ የሆነው ኢኖቫ ፓኬጂንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተጠሪ ለወሰደው ብድር የድርጅቱን ንብረቶች በዋስትና [illegible] ምክንያት የድርጅቱ ንብረቶች ከቀረጥ ነጻ የገቡ በመሆኑ በንብረቶቹ ላይ መንግስት የሚፈልገውን ቀረጥና ታክስ ለመክፈል

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [illegible] ቀን 29-6-14

ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ የቀረጥና ታክስ ክፍያ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የሰጠውም ተጠሪ በህግ አግባብ መክፈል የነበረበትን ቀረጥና ታክስ ባለመክፈሉ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በተጠሪ እና በአመልካች መካከል አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የቀረጥና ታክስ ክፍያ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ የቀረጥና ታክስ እዳ ምክንያት አመልካች ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው የቀረጥና ታክስ እዳት ውሳኔ ላይ በጉምሩክ አ/ቁ 859/06 አንቀጽ 153፣154 እና 155 መሰረት ተጠሪም ሆነ ዋና ባለእዳ ቅሬታቸውን እንደቅደም ተከተላቸው ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤትና ለፌደራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አላቀረቡም፡፡ ይህ ሳይፈጸም በቀጥታ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ውሳኔውን ማጽናቱ የጉምሩክ አ/ቁ 859/2006 አንቀጽ 153፣154 እና 155 ድንጋጌዎችን እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 86817(ቅጽ 15) በ22/1/06ዓ.ም የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ባላገናዘበ ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ አመልካች ያነሳውን መቃወሚያ በአግባቡ ሳይመረምሩ ወደ ፍሬጉዳዩ ገብቶ የሰጠው ፍርድ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 9፣231(1)(ለ) እና 244(2)(ለ) ድንጋጌዎችን የሚጣረስ፣ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ ፍሬጉዳዩን በተመለከተም አመልካች የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚልበትን ምክንያቶች በመዘርዘር ውሳኔው እና ትእዛዙ እንዲሻር እንዲሁም አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የክፍያ ትእዛዝ በአ/ቁ 859/2006 እና የታክስ አስተዳደር አ/ቁ 983/08 መሰረት በአግባቡ ነው ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥ አመልክቷል፡፡

ይህ አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የገባውን ማሽነሪዎች ባንኩ በዋስትና መያዝ አይችልም ህጉ ይከለክላል እያለ አመልካች እየተከራከረ ባለበት ሁኔታ ማሽኖቹን ባንኩ ለ3ኛ ወገን መሸጡና ማስተላለፉ አልተረጋገጠም በሚል የጉምሩክ ኮሚሽን የፈጠረው ሁከት ይወገድ በማለት የስር ፍ/ቤት የወሰነበትን አግባብ ከአ/ቁ 859/06፣ 983/08 እና 60/89 እና ማሻሻያው ቁ 622/01 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ3/2/13ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ16/2/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ የቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የስረነገር ስልጣን የለውም ሲል ያቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን እንዲሁም ወደፍሬጉዳዩ ገብቶ የሰጠው ውሳኔ እና በዚሁ ላይ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚልበትን ምክንያቶች በመዘርዘር ውሳኔው [illegible] እንዲጸና፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለው እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

አመልካች በ7/3/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
29-6-14